# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

፳፮ኛ አመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th year No 62
Addis Ababa July 17, 2018


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፷፪/፪ሺ፲**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ**


**ገጽ...............ሺ፫፻፸፮**


**Content**

**Proclamation No 62 /2018**

**ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT RIVER BASINS AND GREEN AREAD AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION**


**Page …….. 1376**


**አዋጅ ቁጥር ፷፪ /፪ሺ፲**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፪/፪ሺ፲**

የከተማው ተፋሰሶች እና ሌሎች አረንጓዴ አካባቢዎች የከተማው የተፈጥሮ ፀጋዎች አካላት እና የከተማው ሀብት እና ውበት ቢሆኑም፣ በሚፈለገው ደረጃ አለመልማታቸው እያስከተለ ያለውን ችግር በከተማው መዋቅራዊ ፕላን በተመለከተው መሰረት በመመራት መፍታት እና በተሻለ ሁኔታ እንዲለሙና እንዲጠበቁ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

**Proclamation No 62/2018**

**ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT RIVER BASINS AND GREEN AREAS AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION NO.62/2018**

**WHEREAS,** it is imperative to solve the problems that have been emanating from the absence of the desirable level of feasibility of development of the rivers and other green areas which form part of the natural gifts, resources and beauty of the city in pursuance with the structural plan of the city and ensure their development and safekeeping on a better level;


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ
Unit price

ያለአግባብ በመባከን ላይ የሚገኘውን የዝናብ ውሃና ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርስ የቆየውን ጎርፍ ዘመናዊ የልማት አማራጮችን ተጠቅሞ እንደየአግባቡ በማስረግ፣አቁሮ በመያዝና ወደወንዞች እንዲገባ በማድረግ መቆጣጠርና በተሻለ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

**WHEREAS,** it is necessary to create conditions by which modern development alternatives are used to effectively cause running water get absorbed into the ground, containing it by ponds and causing the rest flow properly into rivers in order to control and better exploit rainwater fall that has been improperly wasted and the flood flash that has been causing enormous damage as a result of mismanagement ;

ባለቤት በማጣት እና በስልጣን መደራረብ የተነሳ በተፋሰሶች እና በሌሎች አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት እና አስተዳደር ረገድ የሚታዩ ችግሮችን በሚቀርፍ መልኩ የመዋቅራዊ ፕላኑን እና የስልታዊ ልማት ዕቅድ ማዕቀፉን ቀጣይ ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል አዎንታዊ የአካባቢ ጥበቃ፣ ልማት፣ እንክብካቤ እና አስተዳደር ለማካሄድ ምቹ ተቋማዊ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

**WHEREAS,** it is necessary to create conducive institutional setup that will care out positive environmental conservation, development, safekeeping and administration enabling to successfully realize the mission of the structural plan and the strategic development plan scheme of the city in a manner that helps solve the problems of the lack of a specific responsible body and overlap of powers visible in respect of the development and administration of the river basins and other green areas;

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬(፩)(ሀ) በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

**NOW, THEREFORE,** the Addis Ababa City council has hereby promulgated this Proclamation in accordance with Art. 14 (1) (a) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended).

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## Part One
## General Provisions

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፪/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short title

This Proclamation may be cited as "The Addis Ababa City Government River Basins and Green Areas Agency Proclamation No. 62/2018

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

፩) "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪) "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፫) "የከተማ ስራ አስኪያጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ስራ አስኪያጅ ነው፤

፬) "የከተማ ካቢኔ"ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ነው፤

፭) "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፮) "ኤጀንሲ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 የተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲ ነው፤

፯)"ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የሚመሰረተው የኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ነው፤

፰) "ኮሚሽን" ማለት የከተማው አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ነው፤

፱) "ፕላን/የከተማ ፕላን" ማለት መዋቅራዊ ፕላንና የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲሁም በሕግ የተደነገጉ ሌሎች ፕላኖችን ያጠቃልላል፤

## 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation,

1) "City" means the Addis Ababa City;

2) "Mayor" means the Mayor of the Addis Ababa City;

3) "City manager" means the Addis Ababa City manager;

4) "City cabinet" means the Addis Ababa City cabinet;

5) "City government" means the Addis Ababa City government;

**6**) "Agency" means the Addis Ababa City Government River Basins and Green Areas Agency established by Art. 3 of this Proclamation;

7) "Board" means the managing board of the Agency to be constituted according to this Proclamation;

8) "Commission" means the Addis Ababa City Government Plan Commission;

9) "Plan/urban plan" means that which includes the Addis Ababa City structural plan and local development plan as well as other plans legally adopted;

፲) "መዋቅራዊ ፕላን" ማለት በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ እና በአካባቢያዊ ዘርፎች የተመጣጠነ የከተማ ልማት ለማስገኘት በሚያስችል መልኩ የከተማውን ፊዚካላዊ እድገትና ልማት በተመለከተ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮችን የሚዘረዝርና ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው አብይ የከተማ ፕላን ነው፤

፲፩) "የአካባቢ ልማት ፕላን" ማለት በስልታዊ ባህሪያቸው ምክንያት በተመረጡ አካባቢዎች ላይ በማተኮር የከተማውን አንድ አካባቢ ለማሻሻል፣ለማደስና ለማስፋፋት በመካከለኛ የዕቅድ ዘመን በጊዜ እየተከፋፈሉና እየተቀናጁ የሚከናወኑ የልማት ስራዎችን የሚያሳይና መዋቅራዊ ፕላኑን በተመረጡ አካባቢዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የልማት ግቦችን፣ አበይት ተግባራትን፣ የአፈጻጸም ስልቶችን፣ የፈጻሚ አካላትን ሚና እና ተፈላጊ ተቋሞችን፣ የአካባቢ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴን፣ የከተማ ዲዛይን መርሆዎችን፣ ተጨባጭ መስፈርቶችን፣ የአካባቢ ማዕቀፉን፣ በጀትንና ጊዜን በዝርዝር የሚያሳይ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለውና መዋቅራዊ ፕላኑ ተግባራዊ የሚደረግበት ፕላን ነው፤

፲፪) "መንገድ" ማለት የከተማው መዋቅራዊ ፕላን ክፍል በሆነው የመንገድ እና የመጓጓዣ መረብ ፕላን ተለይቶ የተመላከተ እና/ወይም በኮሚሽኑ በሚዘጋጁ ዝርዝር ፕላኖች የተመላከተ ማናቸውም መንገድ ነው፤

፲፫) "ተፋሰስ/ሶች" ማለት ከተማውን አቋርጠውም ሆነ በከተማው ውስጥ ተወስነው የሚፈሱ ወንዞችንና ወደ ወንዞቹ ውሃ የሚመግቡ አካባቢዎችን እንዲሁም ሰው ሰራሽ ሀይቆችን

10) "Structural plan" means a major urban plan that prescribes requirements to be met concerning the physical growth and development of the city in the manner that brings about balanced urban development in the social, economic and environmental sectors and has legally binding effect;

11) "Local Development Plan" means a specific legally binding plan which depicts medium term, phased, and integrated activities designed to upgrading ,renewing and expanding an urban area with a view to facilitating the implementation of the structural plan by focusing on strategic areas and prescribes development objectives, major activities, implementation strategies, roles of implementing bodies and required institutions, local economic dynamism, urban design principles, concrete requirements, local framework, budget and time needed for the implementation of the structural plan in selected areas;

12) "Street" means any street envisaged by the street and transport network plan forming part of the structural plan and/or detail plans adopted by the Commission;

13) "River Basin/s" means rivers that flow across and end up in the city together with water sources feeding them as well as man-made lakes and the buffer areas surrounding

እና በሁለቱም ጎኖቻቸው በመዋቅራዊ ፕላኑ በሃያ ሜትር ክልል ውስጥ ያሉትን ዳርቻዎቻቸውን ያካትታል፤

፲፬) “አረንጓዴ አካባቢ/ዎች” ማለት በከተማው መዋቅራዊ ፕላን በተመላከተው መሰረት በከተማው ውስጥ የሚገኙ ደኖችን፣ መናፈሻዎችን፣ መካነ እንስሳትን፣የዕፅዋት ማዕከላትን፣የወንዝ ዳርቻዎችን፣ የሕዝብ መናኸሪያዎችን፣ዘላቂ ማረፊያዎችን፣በመንገድ ዳርቻ፣ አካፋይ እና አደባባይ ለአረንጓዴ ልማት የተዘጋጁ ስፍራዎችን እንዲሁም በመኖሪያ ሰፈሮች እና በሌሎች አካባቢዎች ለአረንጓዴ ልማት እና ለሕዝብ የጋራ ጥቅም ተብለው የተወሰኑ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ክፍት ቦታዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፤

፲፭) “ደን” ማለት በከተማው ውስጥ በተፈጥሮ የበቀሉ እና/ወይም ተተክለው የለሙ በአብዛኛው ዛፎች እና ሌሎች የእንጨትነት ፀባይ ያላቸው ተክሎች የሚገኙበት የእጽዋት ክምችት ነው፤

፲፮) “ዕፅዋት” ማለት ማናቸውንም ኢኮኖሚያዊ፣ ከባቢያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ተክሎችን የሚያካትት የጥላ፣የፍራፍሬ እና የጌጥ ዛፎችን፣ ቁጥቋጦችን፣ አበቦችን እና ሳሮችን የሚያጠቃልል ስብስብ ነው፤

፲፯) “ዛፍ” ማለት አንድ ጠንካራ ግንድ ያለው ቋሚ ዕፅ ሆኖ ቁመቱ አምስት ሜትር እና በላይ የሆነ ተክል ነው፤

፲፰) “መናፈሻ” ማለት ለደን ልማት፣ ጥበቃ፣ ውበት፣ ተፈጥሮአዊ መስህብ እና መዝናኛ አገልግሎት ተብሎ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን የተመላከተ እና በተፈጥሮ የበቀሉ እና/ወይም ተተክለው

them within 20 metres on both sides as envisaged by the structural plan;

14) Green area/s” means that which includes forests, parks, zoos, plant centres, river buffers, plazas, cemeteries, places prepared for green development along the sides , divides and squares of streets as well as all open places designated for green development and for communal use within residential neighbourhoods and other areas as envisaged by the structural plan of the city;

15. “Forest” means a spot of collection of plants that consists mostly of trees and other plants of a wooden character that are naturally grown and/or afforested;

16) “Plants” means a collection of plants which includes shade, fruit and ascetic trees, bushes, flowers and grasses having any economic, environmental, cultural and social benefits;

17) “Tree” means a plant that has a strong permanent stem and a height of five metres and above thereof;

18) “Park” means a land use area designated by the structural plan for the purposes of green development, conservation, beautification, natural attraction and recreational values and

የለሙ ዕፅዋት እና/ወይም ዛፎች ያሉበት ሆኖ፣ የሕዝብ መናኸሪያ እና የክብረ በዓል ቦታዎችን፣ የመንገድ አካፋዮችን እና ዳርቻዎችን እንዲሁም አደባባዮችን የሚያጠቃልል እና የሚሰጡትን አገልግሎት መሰረት በማድረግ ሬርጅብዙ መናፈሻ፣ ክልላዊ መናፈሻ፣ ከተማ አቀፍ መናፈሻ፣ ክፍለ ከተማ መናፈሻ፣ የወረዳ መናፈሻ፣ የሰፈር መናፈሻ፣የባሕል እና የታሪክ መናፈሻ፣ ክፍት የሕዝብ መናፈሻ፣የመንገድ ዳር መናፈሻ፣ የሕዝብ መናኸሪያ መናፈሻ፣መካነ እንስሳት መናፈሻ፣የህጻናት መናፈሻ፣ስፖርት ነክ መናፈሻ፣አሚዩዝመንት መናፈሻ ወ.ዘ.ተ. ተብሎ ሊመደብ ይችላል፤

፲፱) “ዘላቂ ማረፊያ” ማለት በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሰረት የሰው አካል ከሕይወት በኋላ እንዲያርፍበት የተመደበ በአረንጓዴነት የለማ ወይም የሚለማ ቦታ ሲሆን፣የቀብር ቦታን፣ፉካን እና የጋራ ማረፊያ ቦታን የሚያጠቃልል ነው፤

፳) “የአረንጓዴ ልማት ደረጃ” ማለት የከተማ ውበት ለማምጣት እና መናፈሻዎችን ለማልማት የሚያስችል ዝቅተኛ ተፈላጊ መስፈርቶችን ዝርዝር መግለጫ ይዞ በከተማው አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተጠንቶ የሚወጣ ሕጋዊ ሰነድ ነው፤

፳፩) “የከተማ ውበት” ማለት በዕፅዋት አተካከል እና እንክብካቤ፣በሕንፃዎች እና አጥሮች ቀለም አቀባብ፣በስነ ሕንፃ ዲዛይን፣ በኤሌክትሪክ እና በውሃ ስራዎች ቅንብር ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ የተፈጠረ ማራኪ የከተማ ገጽታ ነው፤

፳፪) “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

consists in trees or plants that are naturally grown and/or afforested, plaza and festival sites, street sides, divides and squares; and they can be classified as per their services as multifunctional recreational park, regional park, citywide park, sub-city park, district park, neighbourhood park, cultural and historical park, open public park, street side park, open plaza park, plantlogy park, children park, sport based park, amusement park, etc;

19) “Cemetery” means a land use area designated and developed or to be developed as green according to the structural plan of the city for the purpose of placing human bodies after life and includes burial site, burial chamber and collective burial places;

20) "Green development standard" means a legal document developed or to be developed by the Environmental Protection Authority of the City Government envisaging the minimum required criteria designed to bring about urban beauty and develop parks;

21) "Urban beauty" means an attractive urban feature designed and adopted in the form of standard of a landscape for growing and conserving plants, colouring of buildings and fences, architectural design, and combination of electrical and water works;

22) “Person” means any natural person or a juridical body;

፳፫) በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታን ያጠቃልላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኤጀንሲው መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ዓላማ፣ስልጣን እና ተግባር

**፫. መቋቋም እና ተጠሪነት**

፩) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተፋሰስ እና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪) ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

**፬. ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩) በከተማ ፕላን የተቀመጠውን የ30% (የሰላሳ መቶኛ) መጣኔ የአረንጓዴ ልማት ሽፋን ስትራቴጂ ተግባራዊ በማድረግ የከተማው ነዋሪዎችን አማካኝ የነፍስ ወከፍ ተደራሽ አረንጓዴ ሽፋን የማሳደግ፤

፪) ተፋሰሶችን እንደተፈጥሮ ፀጋ በመውሰድ ከተማው ለነዋሪዎች እና ለእንግዶች በአረንጓዴነት እና በውበት ተመራጭ እንዲሆን የማድረግ፤

፫) የተፋሰስ እና የአረንጓዴ አካባቢዎች ልማት፣ ስራ አመራር እና አገልግሎቶች በዘመናዊ የመረጃ ተግባቦትና ሌሎች አማራጮች ተደራሽ እና ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ለተጠቃሚዎች የማመቻቸት፡፡

23) Any provision of this Proclamation rendered in the masculine gender shall also include the feminine gender.

## Part Two

## Establishment, Accountability, Purpose, Powers and Functions of the Agency

**3. Establishment and accountability**

1) The Addis Ababa City Government River Basins and Green Areas Agency is hereby established by this Proclamation as a public office of the city government with legal personality conferred on it.

2) The Agency shall be accountable to the City manager.

**4. Purposes**

The Agency shall have the following purposes:

1) To raise the green cover that amounts to the share of each resident of the city by developing the 30 (thirty) percent ratio green cover development strategy envisaged by urban plan;

2) To ensure that the city becomes choiceable being green and beautiful for its residents and guests by treating river basins as natural gifts;

3) To create conducive conditions for users whereby the development , management and services of river basins and green areas are made available through modern information communication and other alternatives;

## ፭. ስልጣን እና ተግባር

ኤጀንሲው በስራው መስክ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩) የጉለሌ እጽዋት ማዕከልን፣ የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከልን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንበረት ለውጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ፅሕፈት ቤትን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንጦጦ እና አከባቢው የቱሪስት መዳረሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን፣ እና የአዲስ አበባ መናፈሻዎች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እያንዳንዱ ተቋም የተቋቋመበትን ሕግ ላጸደቀው አካል በማቅረብ ያስወስናል፣ በሚወሰነው መሰረትም ይፈጽማል፡፡

፪) የከተማው ተፋሳስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማትን በተመለከተ እያጠና የፌደራል መንግስትንና የከተማውን አስተዳደር ፖሊሲዎችና ሕጎች አላማዎች የሚያሳኩ የፖሊሲ ሐሣቦችን፣ ሕጎችን፣ መርሀ ግብሮችን፣ ስትራቴጂና የአፈጻጸም መመሪያ እንዲሁም የሚመራቸውን የመንግስት ተቋማት ዕቅድና በጀት የሚያካትት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ያቀርባል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ እንዲሁም በሚመራቸው አካላት እንደየአግባቡ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

## 5. Powers and functions

The Agency shall have the following powers and functions in its purview of engagement, and it shall:

1) Oversee, coordinate and control the Gulele Botanical Garden, Addis Zoo-Park Centre, Addis Ababa City Government Rivers and river sides Development and Climate Change Adaptation Project Office, Addis Ababa City Government Entoto and its Surrounding Tourist Destination Development Project Office, and Addis Ababa Parks Development Project Office.; And, where reorganization is Found necessary, it shall submit its proposal to the appropriate organ that has endorsed the legislation for the establishment of each institution and implement same when so decided ;

2) Study concerning river basins and green areas and prepare and forward policy ideas, laws, programs, strategies and implementation guidelines as well as its annual activity and budgetary plan consisting of the activities and budgetary appropriations of the institutions it oversees in a way that promotes the purposes of the policies and laws of the federal government and of the city government; it shall also implement same upon approval, thereof by the concerned organ and ensure the implementation of same by the institutions;

፫) በከተማው ፕላን የተመላከቱ አረንጓዴ አካባቢዎችን በየአይነታቸው በዝርዝር ይለያል፣ የይዞታ ማስረጃ ሊወጣላቸው የሚችሉትን በሚመለከተው አካል በስሙ በማስመዘገብ የይዞታ ምስክር ወረቀት ያወጣል፤

፬) ተፋሰሶችን እና አረንጓዴ አካባቢዎችን ያስከብራል፣ ይጠብቃል፤ በተፋሰሶች እና በአረንጓዴ አካባቢዎች በፕላንና በዲዛይን ያልተደገፈ ልማት እንዳይካሄድ፣ የተካሄደም ካለ በሕግ መሰረት እንዲወገድ ያደርጋል፤

፭) የተፋሰሶችን እና የአረንጓዴ አካባቢዎችን ቅደም ተከተል በማውጣት የልማት ወይም መልሶ የማልማት ዝርዝር ፕሮጀክት ያዘጋጃል፣የተቀናጀ የአረንጓዴ ልማት ቦታ አቀማመጥ ዲዛይን በማዘጋጀት ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል ወይም እንዲተገበር ያደርጋል፤

፮) ተፋሰሶችን እና አረንጓዴ አካባቢዎችን በጸደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን መሰረትና የጸደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን በሌላቸው አካባቢዎች ደግሞ በመዋቅራዊ ፕላኑ አግባብ ያላቸው ክፍሎች በተመለከተው የአረንጓዴ ሽፋን መጣኔ መሰረት የልማት ደረጃ ጠብቆ ወይም አስጠብቆ ያለማል፣ ወይም እንዲለማ ያደርጋል፤እንዲሁም ለወንዝና ለደን ስፍራነት መዋል የሚገባቸው ተጨማሪ ቦታዎች በማጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም እንዲለሙ ያደርጋል፤

፯) የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ግንባታ ዲዛይን አካል አድርጎ በሚያዘጋጃቸው የመትከያ ስፍራዎች ዲዛይን መሰረት በዋና

3) Identify in detail the green areas designated by the urban plan according to their types and obtain from the concerned organ title deeds in its name for the green areas which are eligible thereto;

4) Secure and protect river basins and green areas and ensure that a development is not undertaken without plan and design, as well as lawfully cause the removal of constructions undertaken illegally;

5) Sort out, study and prepare specific projects of the development or redevelopment of river basins and green areas, prepare and submit to the Commission integrated land escape designs of green areas and implement or ensure the implementation of same when approved;

6) Develop or ensure the development of river basins and green areas in conformity with the respective green development standard to the extent of the green cover ratio envisaged by local development plan or, where a local development plan has not been adopted, by the relevant component parts of the structural plan, and identify through studies and propose additional areas that should be designated for rivers and forests and ensure their development when so decided;

7) Grow and cultivate or ensure the growing and cultivation of appropriate shade trees on both sides, divides and squares of arterial and

መንገዶች እና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮች እና አደባባዮች አግባብ ያላቸውን የጥላ ዛፎች ይተክላል፣ ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፣ ይንከባከባል፣ ይጠብቃል፤

፰) የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርዱ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳር፣ አካፋይ እና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈላጊነቱ ያስወግዳል ወይም ይመለምላል፤

፱) በሚመራቸውና በሚያስተባብራቸው የመንግስት ተቋማት ከሚከናወነው በተጨማሪ የከተማውን አየር ሚዛን የሚጠብቁ እንዲሁም ለከተማው ውበትና መናፈሻ ልማት የሚውሉ የዛፍ ችግኞች፣ የአበባና የዛፍ ዝርያዎች የሚባዙባቸውን የችግኝ ጣቢያዎች ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ችግኞችን ለተጠቃሚዎች በሽያጭም ሆነ በስጦታ ያቀርባል፤ እንዲሁም በከተማው ውስጥ መልማት ያለባቸው በላቀ ሁኔታ ውጤታማ የሆኑና ያልታወቁ ወይም ያልተሞከሩ የውጭ እና ሀገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎችን በማጥናት የሚለሙበትን አግባብ በሕግ መሰረት ያስተዋውቃል፤

፲) የለሙ ተፋሰሶችንና አረንጓዴ አካባቢዎችን ይንከባከባል፣ ያስተዳድራል፤ በሚመራቸውና በሚያስተባብራቸው የመንግስት አካላት የሚካሄዱ የማልማትና የስራ አመራር ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩) የሠፈር ቁርጥራጭ ክፍት ቦታዎች በሠፈሩ ነዋሪዎችና እንደየአግባቡ በሌሎች ባለድርሻዎች

sub arterial streets according to the design prepared by the Addis Ababa City Road Authority as integral part of the design of the construction of streets;

8) Remove or prune, where necessary, plants that block the long sight of drivers or are dried on the sides, divides or squares of streets;

9) Expand and administer seedling stations, other than those under the institutions it oversees and coordinates, where tree seedlings and peculiar types of seeds of flowers and trees that balance the climate of the city as well as are usable for the beautification of the city and development of the parks of the city, supply for users seedlings either by sale or free of charge, and identify through study and publicize, according to law, the means and ways of cultivating exceedingly productive but unknown or untested types of external and domestic plants that must be grown in the city;

10) Look after and administer developed river basins and green areas, and ensure that development and management activities are undertaken properly by the institutions it oversees and coordinates;

11) Cause the development, cultivation and protection or safekeeping by the respective

ቀጥተኛ ተሳትፎ የከተማው አረንጓዴ ልማት አካል ሆነው እንዲለሙ ያደርጋል፣ ይንከባከባል፣ ይጠብቃል፣ ወይም ያስጠብቃል፤ ለዚህ አላማም የሠፈር ነዋሪዎች በተለያየ መልኩ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፤

፲፪) በተፋሰስና በአረንጓዴ አካባቢዎች ልማትና አገልግሎት ዘርፎች መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች ፣የሃይማኖት ድርጅቶች፣የሰፈር ነዋሪዎች ወይም ሌሎች አካላት በየበኩላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄና የልማት ዕቅድ መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፤የአረንጓዴ ልማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፫) የዝናብ ውሃ በተፋሰስ መነሻ ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲሰርግ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤ ተፋሰስን ተከትሎ ውበትን ከአረንጓዴ ልማት ጋር በማስተሳሰር የከተማው የተፈጥሮ ጸጋ አካል ሆኖ እንዲለማ ጥናት ያካሂዳል፣ ዲዛይን በማዘጋጀት ይተገብራል፤ መወገድ ያለበት የዝናብ ውሃ አደጋ ሳያስከትል የሚወገድበት ዲዛይን በማዘጋጀት ማስወገጃ መስመር ይገነባል፣ ትርፍ ውሃ በተገነባው መስመር እንዲወገድ ያደርጋል፤

፲፬) የተፋሰስና የአረንጓዴ አካባቢ ማልማትና ስራ አመራር በውክልና ወይም በውል መሠረት እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፣ ይቆጣጠራል፤

residents of open detached spaces located within neighbourhoods as part of the greenery of the city and, where appropriate, by maximizing the direct participation of other stakeholders; to this end, it shall also support and coordinate residents so that they are organized and mobilized in their respective neighbourhoods;

12) Issue green development permit to private proprietors, religious organizations, neighbourhood residents or other institutions desiring to do so by examining their respective requests and development plans, and issue, monitor and control green development competence certificate;

13) Conduct studies that enable to utilize or absorb rainwater on the upper streams of river basins and implement the findings thereof, conduct studies with a view to interrelating beautification with green development as part of the natural gifts of the city along river basins and implement or ensure the implementation of same, and construct drainage outlets according to designs it prepares and remove, through the drainage outlets, extra rainwater that is no longer required;

14) Ensure that works of development and management of green areas by outsourcing or delegation wherever and control the conduct thereof;

፲፭) የአገልግሎት ክፍያ ተመን ደንብ በማዘጋጀት ለከተማው ስራ አስኪያጅ ያቀርባል፣ በከተማው ካቢኔ ሲጸድቅም ለሚሰጠው አገልግሎት በተመኑ መሠረት ያስከፍላል፣ገቢ በማድረግ በሕግ መሰረት ይጠቀማል፤

፲፮) የለሙ ወይም በቀጣይ የሚለሙ የተፋሰስና የአረንጓዴ ልማት አገልግሎቶች በቂ ገቢ በማመንጨት ወጪያቸውን መሸፈንና ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት ከሚችሉበት አቅም ላይ እንዲደርሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የራሱን ወጪ መሸፈንና ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት የሚችለውን እያንዳንዱን አገልግሎት እያጠና በስራ አመራር ቦርዱ እንዲመከርበት ካደረገ በኃላ የልማት ድርጅት ሆኖ ወይም በሌላ መልኩ እንዲተዳደር ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ይፈፅማል፤

፲፯ ተፋሰሶችንና አረንጓዴ አካባቢዎችን የሚመለከቱ የፌደራልና የከተማው አስተዳደር ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎችና ስልቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፲፰) የሕዝብ ተግባቦትና ስርፀት እንዲሁም የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያከናውናል፤ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ስነዳና ስርጭት ቋት ያደራጃል፣ጥቅም ላይ ያውላል፤

15) Prepare and submit to the City Manager service charges rates Regulations, exact charges for the services it renders when the Regulations approved by the City Cabinet, handle same as revenues and make use of same according to law;

16) Undertake to provide the necessary support to enable developed or planned services of river basins and green areas reach out for the capacity of covering their expenses by generating their own revenues and further boosting same; and it shall also study and, having consulted the Board, propose a certain service having such a capacity to be incorporated as a public enterprise or established differently and act as necessary upon the decision thereof;

17) Ensure the implementation of laws, policies, standards and strategies of the federal government and the city government concerning river basins and green areas;

18)Undertake to carry out public communication and conscisoutization as well as study and research; organize documentation and information publicity database by employing accessible modern user friendly information communication technology and make it available for use.

፲፱) ሠራተኞቹን በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ እንዲሁም የዋናና የምክትል ዋና ዳይሬክተሮቹም ሆነ የሚመራቸውና የሚያስተባብራቸው ተቋማት ኀላፊዎች የሥራ ሁኔታ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የተወሰነው ይሆናል፤

፳) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

፳፩) ከሌሎች የከተማ ፕላን ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ጋር እንደአስፈላጊነቱ በሕግ መሰረት ተባብሮ ይሠራል፤ ኮሚሽኑ ወጥነት ያለው የከተማ ፕላን አፈጻጸም ለማረጋገጥ የሚሰጠውን አቅጣጫ፣ ድጋፍና ምክር በመቀበል በከተማው ፕላን መሰረት ይፈጽማል፣ ያስፈፅማል፤

፳፪) ለሥራው እንቅስቃሴ ስኬታማነት ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ የፌዴራልና የክልል አግባብ ያላቸው ተቋማት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የመስኩ የምርምርና ስርፀት ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፳፫) በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ፕላኖች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና የወጣቶች ጉዳዮች እንዲካተቱ ያደርጋል፤

19) Employ, administer and fire its public servants according to the Public Servants administration law, and the working conditions of the executive and deputy executive directors as well as the heads of the institutions it oversees and coordinates shall be those which are determined by the appropriate law;

20) Undertake to carry out capacity building functions, and execute reform and good governance functions and ensures their result-orientedness;

21) Undertake to work according to law in cooperation with other organs that implement urban plan, and implement the urban plan and ensure the implementation of same by receiving direction, support and advice that the Commission renders with a view to ensuring the consistent implementation of the urban plan;

22) Undertake to work in collaboration with appropriate institutions of the federal and regional governments , higher education, research and sensitization institutions that may contribute for the successful realization of its functions and responsibilities;

23) Ensure the mainstreaming of the affairs of women and youth in the policies, laws, plans, development programs and projects it prepares;

፳፬) አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና የማህበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ቫይረስ ያለባቸው ሰዎች በተፋሰሶችና በአረንጓዴ አካባቢዎች የሚካሄዱ ግንባታዎች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች ተደራሽ ሆኖላቸው ጭምር የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳፭) በሕግ መሰረት ውል ይዋዋላል፤ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ያስተዳድራል፣ ያስወግዳል፤ ሊከሰስ ወይም ሊከስ ይችላል፤

፳፮) የቦርዱ ፅሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፳፯) በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የስልጣን አካላቱ ተግባር እና ኃላፊነቶች</u>**

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ድርጅታዊ መዋቅር፣የዋና መስሪያ ቤት እና የቅርንጫፍ መስሪያ ቤት መቀመጫዎች</u>**

**፮. <u>ድርጅታዊ መዋቅር</u>**

ኤጀንሲው የሚከተለው ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል፡-

፩) ስራ አመራር ቦርድ፣

፪) በከንቲባ የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣

፫) በከንቲባው የሚሾሙ ምክትል ዋና

24) Create conducive conditions by which constructions within the bounds of the services of river basins and green areas can be made accessible to persons with disabilities, elderly people and other sections of the society who are vulnerable to social and economic problems as well as persons having HIV/AIDS in their blood and they can become users of equal opportunity and full participants;

25) Conclude contracts; own, administer and dispense property; and may sue or be sued in its name according to law;

26) Undertake to serve as the secretariat of the Board and provide the Board with the necessary support;

27) Undertake to carry out other powers and functions conferred on it by other laws.

**<u>Part Three</u>**

**<u>Organizational Structure of the Agency and Functions and Responsibilities of Its power organs</u>**

**<u>Chapter One</u>**

**<u>Organizational Structure and the Seat of the Head quarters and Branch Offices</u>**

**6. <u>Organizational Structure</u>**

The organizational structure of the Agency shall be the following:

1) Managing board;

2) Executive director appointed by the Mayor;

3) Deputy executive directors appointed by the Mayor;

፬) አስፈላጊ የስራ ዘርፍ አደረጃጀቶች፣ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችና የሰው ሀብት።

**፯. <u>የዋና መሥሪያ ቤት እና የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች መቀመጫ</u>**

፩) የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በከተማ ውስጥ አመቺና ተደራሽ በሆነ ስፍራ የሚቀመጥ ይሆናል።

፪) የኤጀንሲው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ኤጀንሲው በከተማው ውስጥ የሚያለማቸውና የሚያስተዳድራቸው ተፋሰሶች እና አረንጓዴ አካባቢዎች ተጠቃሚ የከተማው ነዋሪዎችን ብዛት ከግምት በማስገባት በልማት እና በአገልግሎት አሰጣጥ ምቹት እና ተደራሽነት መርህ መሰረት ተደራጅተው በየአካባቢው የሚኖራቸው መቀመጫ ይወሰናል።

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የቦርዱ አመሰራረት፣ ኃላፊነት እና አሰራር ስነስርዓት</u>**

**<u>፰. የቦርዱ አመሰራረት እና የአባላቱ አሰያየም</u>**

፩) ቦርዱ ሰባት ወይም ዘጠኝ የሚሆኑ አባላት ይኖሩታል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቦርዱ አባላት ብዛት በከንቲባው በሚወሰነው መሰረት ሊጨምር ይችላል፤

፪) ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ አባል እና ጸሐፊ ይሆናል፤

፫) የከተማው ስራ አስኪያጅ ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በመመካከር ሙያዊና ቅንጅታዊ አግባብን ከግምት



4) Necessary structures of work divisions, projects and required human resource.

7. **<u>Seat of Head Quarters and Branch Office</u>**

1) The seat of the Head quarters of the Agency shall be made at a conducive and accessible venue in the city;

2) The seats of the branch offices of the Agency shall be located based on the principles of convenience, availability, accessibility and other relevant factors of the developments and services of river basins and green areas that the Agency shall organize and manages by taking into account the number of users.

**<u>Chapter Two</u>**

**<u>Formation, Powers and Operational Procedures of the Board</u>**

**8. <u>Formation and Designation of the Members of the Board</u>**

**1)** The board shall have seven or nine members; where it is found necessary; however, the number of the members of the Board may increase according to the decision of the mayor.

2) The executive director of the Agency shall be a member and the secretary-general of the board

3) Other members of the Board, including the chairperson shall be designated by the Mayor based on the shortlist of candidates that the

አስገብቶ የሚያቀርበውን የእጩዎች ዝርዝር መሰረት በማድረግ የቦርዱ ሰብሳቢ እና አባላት አግባብ ካላቸው የከተማው አስተዳደር እና ሌሎች አካላት መካከል በከንቲባው ይሰየማሉ፤

፬) የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውም የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ከአንድ ጊዜ በላይ በአባልነት ሊሾም ይችላል፤

፭) የቦርዱ አባላት እና ሰብሳቢ የከተማው ካቢኔ በሚወስነው መሰረት አበል ይከፈላቸዋል፡፡

**፱. የቦርዱ ተግባር እና ኃላፊነት**

፩) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የተሰጡት ስልጣን እና ተግባሮች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በጥቅል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ) ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የኤጀንሲውን ድርጅታዊ መዋቅር፣የሰው ሀብት ፍላጎት፣ ደወመዝና ጥቅማጥቅም መርምሮ ምክረ ሐሳቦችን በመስጠት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲፀድቅ ይወስናል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ስትራቴጂካዊ እቅድ፣ መርሃ ግብር እና ዓመታዊ ዕቅድ እና በጀት መርምሮ ምክረ ሐሳቦችን በመስጠት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲፀድቅ ይወስናል፣ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

City Manager prepares and submits inconsultation with the Executive director by taking into account the professional and coordination appropriateness thereof;

4) The term of office of the members of the board shall be five years; where necessary, however, any board member, including the chairperson may be appointed more than once.

5) The chairperson and other members of the board shall be paid allowances as per the decision of the City Cabinet.

**9. Functions and Responsibilities of the Board**

1) Without prejudice to the powers and responsibilities given to the executive director under Art. 12 of this Proclamation, the board shall oversee the Agency.

2) Without prejudice to the provisions of Sub-Art. (1) of this Article, the board shall:

A) Examine and forward its recommendations on the organizational structure, human resource requirement, salaries and benefits of the Agency presented to it, decide thereon to be referred approval by the concerned organ of the City Government, and monitor its implementation following the approval thereof;

B) Examine, forward its recommendations and decide on the strategic plan, program, annual action plan and budget of the Agency, ensure the submission to and approval thereof by the concerned organs of the City Government, and monitor its implementation following the approval thereof;

ሐ) የኤጀንሲውን ወቅታዊ የስራ ዕቅድ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርቶችን እንዲሁም የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ተገቢውን አመራር ይሰጣል፤ የከተማው ነዋሪዎች እና የሚመለከታቸው አካላት በኤጀንሲው የሥራ እንቅስቃሴ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ ተገቢውን አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

መ) ኤጀንሲው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የበላይ አመራር ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፲. <u>የቦርዱ ስብሰባ ሥነ-ስርዓት</u>

፩) ቦርዱ በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው በሚደረግ ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪) ከስብሰባው ሶስት ቀን በፊት የቦርዱ ስብሰባ አጀንዳ ለአባላት ከማድረስ ጋር የቦርዱ ስብሰባ ጥሪ ይተላለፋል፤አጀንዳ ማስያዝ የሚፈልግ አባል አጀንዳውን በስብሰባ ላይ ማስያዝ ይችላል፤

፫) በቦርዱ ስብሰባ ላይ ቢያንስ ሃምሳ አንድ ከመቶ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

፬) የቦርዱ ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ወይም በአብላጫ ድምጽ የሚተላለፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል ከሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤

C) Examine the periodic work and financial performance reports and audit reports of the Agency and render the appropriate oversight thereon, set out the direction by which the residents of the city and other concerned bodies participate in the operations of the Agency and ensure the implementation thereof;

D) Carry out other related oversight activities that help the Agency to realize the purposes for the achievement for which it is established.

**10. <u>Procedures of the Meetings of the Board</u>**

1) The board shall meet once every three months; it may, however, meet any time upon the call of the chairperson wherever it is found necessary.
2) The call for a meeting of the board shall be communicated to members together with its agenda before three days, and a member who has agenda item/s may propose same in the meeting.
3) The attendance of, at least, fifty-one per cent of the members shall constitute the quorum of a meeting.
4) The decision of the board shall be passed by unanimous or majority vote; if however, the votes tie, the motion voted for by the chairperson shall become the decision of the board.

፭) በቦርዱ የሚተላለፍ ውሳኔ ሕግን የጣሰ ሆኖ ሲገኝ፣ በውሳኔው ተካፋይ የሆነ ማንኛውም የቦርዱ አባል በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ይሆናል፤ ሆኖም የልዩነት ሐሳቡን ያስመዘገበ አባል ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል፤

፮)የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ይደረጋል የስብሰባ አጀንዳዎች ውሳኔዎችና ተዛማጅ ጉዳዮች አስተዋጽኦ በጽሑፍ እየተዘጋጀ ቃለ ጉባኤ ጸድቆ ከተፈረመ በኃላ ለእያንዳንዱ አባል እንዲደርሰው ይደረጋል፤

፯) በዚህ አንቀጽ እና በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቦርዱ ስለ አሰራሩ የራሱን ውስጠ ደንብ በማውጣት ይሰራል፡፡

## ፲፩. የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባር እና ኃላፊነት

የቦርዱ ሰብሳቢ፡-

፩) ቦርዱን በሊቀመንበርነት ይመራል፣የስብሰባ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ቦርዱን ይወክላል፤

፪) የቦርዱ ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ሲያስፈልግ፣ ጥሪው ለአባላቱ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

፫) የቦርዱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፬) የቦርዱ ውሳኔዎችና ሰነዶች በቦርዱ ጸሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

5) Where a decision of the board violates law, a member who has participated in the decision-making shall be accountable individually or jointly; however, a member who has dissented and recorded it in the minutes shall be made free from accountability;

6) The minutes of a meeting of the board shall be recorded, approved and signed by all attendants; and then a concise written note containing the agenda, decisions and other relevant matters shall be prepared and distributed to each member.

7) Without prejudice to the provisions of this Article and other appropriate law, the board may function by adopting its own rules of procedure.

## 11. Functions and Responsibilities of the Chairperson of the Board

The chairperson of the board shall:

1) preside over the board, ensure that a meeting call is announced, and chair the meetings of the board, and represent the board in its relations with third parties;

2) Ensure that the meetings of the board are conducted timely and extraordinary meeting is called wherever it is found necessary,

3) Ensure that the decisions of the board are implemented;

4) Monitor that the decisions and documents of the board are recorded and kept properly by means of the secretary of the board.

## ምዕራፍ ሶስት
## የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር/ሮች ተግባርና ኃላፊነት

### ፲፪ የዋና ዳይሬክተሩ ተግባር እና ኃላፊነት

፩) ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ፣የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ኤጂንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በጥቅል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) የኤጀንሲውን ስልጣን እና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ መርሃ ግብር እና ዓመታዊ የስራ ዕቅድ እና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ በቦርዱ ተመክሮበት በሚወሰነው መሰረት ለሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሐ) የኤጀንሲውን ወቅታዊ የስራ ዕቅድ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርቶች እና ኦዲት ሪፖርት ለቦርዱ እና ለከተማው ስራ አስኪያጅ እንዲሁም ለከተማው አስተዳደር ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሕግ መሰረት ያቀርባል፤

መ)ዓላማዎቹንና የስራ ድርሻውን አፈፃፀም ለማቀላጠፍ የሚያስችለውን ብቃት ያለው የሰው ሃብት በአስፈላጊው የሙያ ጥንቅር እና ብዛት

## Chapter Three
## Functions and Responsibilities of the Executive Director and Deputy Executive Director/s of the Agency

### 12. Functions and Responsibilities of the executive Director

1) Being accountable to the City Manager, the executive director shall be the chief executive officer of the Agency and manage and administer the Agency.

2) Without prejudice to the stipulation of Sub-Art. (1) of this Article, the executive director shall:

(a) Execute the powers and functions of the agency;

(b) Prepare and submit to the board the strategic plan, program, annual action plan and budget of the Agency, submit same to the concerned organ of the City Government according to the consultations and decisions thereon by the board and implement and ensure the implementation of same when approved;

(c) Prepare and submit, as per the law, to the board and the City Manager as well as to the Finance and Economic Development Bureau of the City Government the periodic work performance and financial reports as well as audit report;

(d) Prepare and submit to the board the organizational structure, human resource requirements, attractive and rewarding scheme of job grades and remuneration

ከገበያ ማግኘት የሚያስችለውን ማራኪና አትጊ የደረጃና የክፍያ ስርዓት ከግምት የሚያስገባ የኤጀንሲውን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ሃብት ፍላጎት፣ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም አጥንቶ በማዘጋጀት ለቦርዱ አቅርቦ በሚወሰነው መሰረት ለሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) ኤጀንሲው የሚመራቸውን ተቋማት ኃላፊዎች በመመልመል ለከተማው ስራ አስኪያጅ ያቀርባል፤ ሲሾሙም፣ እያንዳንዱ የሚመራውን የስራ ዘርፍ አደረጃጀት ወይም አካል እንደየአግባቡ ለይቶ በፅሑፍ ይመድባል በበላይነት አቀናጅቶ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ) የኤጀንሲውን ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ የደረጃ ዕድገት እና ስንብት በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ይወስናል፤

ሰ) አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የኤጀንሲውን በጀት የባንክ ሂሳብ በመክፈት ያንቀሳቅሳል፤ ሂሳቡን በጣምራ የሚያንቀሳቅሱ የኤጀንሲውን ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ለይቶ ይሰይማል፤ የገንዘብ ወጪ እንዲከናወን ያደርጋል፣ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣እንዲሁም የኤጀንሲውን ገንዘብና ንብረት አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር ሕግ መሰረት ያስተዳድራል፤

scales aimed at inviting from the labour market the competent human resources in the appropriate professional composition and number required to expedite the achievement of the purposes and mandates of the Agency ,submit it to the concerned organ of the City Government according to the decision of the Board, and implement same when approved;

(e) Select and propose to the City Manager candidate for the heads of the institution the Agency oversees for appointment, assign each appointee in writing to the institution for which he/she is appointed, oversee and control them in coordination with one another ;

(f) Decide, as per the Public Servants law of the City Government, on the employment, assignment, promotion and dismissal of the rest under heads and other staff of the Agency;

(g) Open and operate bank accounts for the operation of the budget of the Agency according to the appropriate finance administration law of the City Government, designate the under heads or staff of the Agency who jointly sign and operate the bank accounts thereof, ensure that money is withdrawn and disbursed properly, and administer the property and assets of the Agency according to the appropriate law of the City Government;

ሸ) የኤጀንሲውን ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እና ሌሎች ተቋማት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ያቀናጃል፤ማናቸውም የኤጀንሲው ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት በአገልግሎቱ ከሚሸፈን/ኑ የአስተዳደር እርከን/ኖች የአመራር አካላት ጋር በአስፈላጊው የሥራ መደጋገፍና ቅንጅት መስራቱንና በኤጀንሲው የስራ ዕቅድ ዝግጅት እና አተገባበር ረገድ ውሳኔ የሚሹ ቴክኒካዊና ሙያዊ ጉዳዮች በኤጀንሲው በየደረጃው መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፤በሕግ መሠረት ውል ይዋዋላል፤

በ) የኤጀንሲውን ዓላማ ለማሳካት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በአጋርነት ይሰራል፤

ተ) የቦርዱ አባል እና ጸሐፊ ሆኖ ይሰራል፤የቦርዱ መረጃዎች፣ ሰነዶች እና ቃለጉባኤዎች በአግባቡ ተደራጅተው እንዲያዙ እና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ ከሰብሳቢው ጋር ተመካክሮ የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች በማዘጋጀት ከስብሰባው ቢያንስ ሦስት ቀን በፊት ለአባላቱ እንዲደርሱ ያደረጋል፡፡

፫) ዋና ዳይሬክተሩ ከተግባር እና ኃላፊነቱ በመቀነስ በኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት ለኤጀንሲው የበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

(h) Oversee the operations of the branch offices and other institutions of the Agency and ensure their mutual synergy and working in the required collaborative engagement and synergy with the organs of the management of the administrative stratum/strata where its services address, and decisions are made at any level of the Agency on matters that require technical and professional considerations regarding the preparation and implementation of the plans of the Agency.

(i) Represent the Agency in its dealings with third parties and conclude contracts according to law;

(j) Work in partnership with appropriate organs in order to ensure the achievement of the purposes of the Agency;

(k) Act as a member and secretary of the board and ensure that the information, documents and minutes of the board are properly organized and safe kept, and prepare meeting agenda in consultation with the chairperson of the Board and ensure that the agenda are included in the call for each meeting and is delivered to members at least three days before the meeting takes place.

3) The Executive director may delegate to the under heads of the Agency part of his functions and responsibilities in accordance with the organizational structure thereof.

**፲፫. የምክትል ዋና ዳይሬክተር ተግባር እና ኃላፊነት**

፩) ኤጀንሲው በድርጅታዊ መዋቅሩ በሚወሰነው መሰረት አስፈላጊ የስራ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፡፡

፪) በስራ ዘርፉ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ፣እያንዳንዱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፡-

ሀ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚመደብበትን የስራ ዘርፍ በኃላፊነት ይመራል፤

ለ) ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው የጽሑፍ ውክልና መሰረት ተክቶት ይሰራል፤

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ኤጀንሲውን የሚመለከቱ እና በኤጀንሲው የሥልጣን ክልል የሚገኙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፲፬. የበጀት ምንጭ**

የኤጀንሲው በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚውጣጣ ይሆናል፡

፩) በከተማው አስተዳደር የሚመደብ በጀት፤

፪) የኤጀንሲው የራሱ ገቢ፤እና

፫) ከተለያዩ ሌሎች ሕጋዊ ምንጮች የሚገኝ ገቢ፡፡

**13. Functions and Responsibilities of Deputy Executive Director**

1) The Agency shall have the required work wing deputy executive directors specified by its organizational structure.

2) Being accountable to the executive director in respect of the wing of the work for which he is responsible, each deputy executive director shall:

a) Manage and be responsible for the operations of the wing of the work to which he is assigned;

b) Replace and work in the shoes of the executive director where the latter is away from office and represent him in writing to do so;

c) Perform such other functions pertaining to the Agency and within the purview of the powers of the Agency as are given to him by the executive director.

**Part Four**

**Miscellaneous Provisions**

**14. Sources of Budget**

The budget of the Agency shall be derived from the following sources:

1) Budget to be allocated by the City Government;

2) Revenues of the Agency; and

3) Rrevenues to be solicited from other different legal sources.

**፲፭. የሂሳብ መዝገብ**

፩) ኤጀንሲው ትክክለኛ እና የተሟሉ የሒሳብ መዛግብትን አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት ይይዛል፣ይጠብቃል፤

፪) የኤጀንሲው የሒሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ የከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር በሚመድበው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

**፲፮. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

፩) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፫ (እንደተሻሻለ)፡-

ሀ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውበት፣ መናፈሻ እና ዘላቂ ማረፊያ ልማት እና አስተዳደር ኤጀንሲን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

ለ) ለከተማው አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአንቀፅ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) የተሰጡት ስልጣን እና ተግባሮች እንዲሁም በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፲) ስር "ለደን እና ለወንዝ ዳርቻ ስፍራነት መዋል የሚገባቸው ተጨማሪ ቦታዎችን በማጥናት ያቀርባል፤ ሲወሰንም እንዲለሙ ያደርጋል" የሚለው ተግባር በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

**15. Records of accounts**

1) The Agency shall maintain and keep accurate and full records of accounts as per the appropriate financial administration law of the City Government ;

2) The records of accounts and documents pertaining to the finance of the Agency shall be audited annually by the auditor to be assigned by the Chief Auditor of the City Government.

16. **Repealed and inapplicable laws**

1) The following provisions of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Organs Reestablishment Proclamation No. 35/2011 (as amended are hereby repealed by this Proclamation:

a) The provisions concerning the Addis Ababa City Government Beautification, Parks and Cemeteries Development and Administration Agency;

b) Powers and responsibilities given to the Addis Ababa City Government Environmental Protection Authority by Sub-Articles (8) and (9) of Article 11, and the provision under Sub-article (10) of Article 11which reads: study and present additional places that deserve to be designated for forests and river buffers and ensure the development thereof when approved`.

፪) ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሕጎች ውስጥ ከኤጀንሲው ስልጣን እና ተግባር ጋር የሚቃረኑት የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተሽረዋል፡-

ሀ) የአዲስ ዙ-ፓርክ ማዕከል ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፶፪/፪ሺህ፬ አንቀጽ ፪(፫)፣ ፬(፪) እና ፮(፩)፣፯(፲፩)፣፰(፮) እና (፯) እንዲሁም የደንቡ ክፍል ሶስት እና በስሩ የተደነገጉት አንቀፆችም ሆኑ በሌሎች አንቀፆች “ቦርድ” የሚለው ቃል፤

ለ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንጦጦና አካባቢው ቱሪስት መዳረሻ ልማት ፕሮጀክት ፅሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፱/፪ሺህ፯ አንቀፅ ፫(፪) እና አንቀፅ ፱-፲፩ እንዲሁም በደንቡ ሌሎች አንቀፆች “በቢሮ፣ለቢሮው፣ቢሮው” እንዲሁም “ቦርድ ወይም አማካሪ ቦርድ” የሚሉት ቃላት፤

ሐ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ፅሕፈት ቤት ደንብ ቁጥር ፸፭/፪ሺህ ፯ አንቀፅ ፭(፪)፣ ፱እና፲ እንዲሁም በሌሎች አንቀፆች "ቦርድ" የሚለው ቃል፤

መ) የአዲስ አበባ ከተማ መናፈሻዎች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፬/፪ሺህ፰ አንቀጽ ፭(፩) እና አንቀፅ ፰-፲ እንዲሁም በደንቡ ሌሎች አንቀፅች "ቦርድ/ለቦርዱ" የሚለው ቃል፤

2) The provisions of the following legislations which are in conflict with powers and functions of the Agency are hereby repealed:

a) Articles 2(3),4(2) ,6(1) and 7(11), 8 (6) and (7),Part Three of the Regulations and the Articles contained therein, as well as the term “Board” in other Articles of the Addis Zoo-Center Establishment Regulations No. 52/2012;

b) Article 3 (2) and 9-11 as well as the terms, “Bureau/to the Bureau, Board/Advisory Board ” under other Articles of the Addis Ababa City Government Entoto and Its Surrounding Tourist Destinations Development Project Office Regulations No. 69/2015;

c) Article 5(2), 9 and 10 as well as the term, “Board” under other Articles of the Addis Ababa city Government Rivers and River sides Development and Climate Change Adaption Project Office Regulation No.75/2015

d) Articles 5 (1), 8 up to 10 and the term "Board/to the Board” under other Articles of the Addis Ababa City Government Parks Development Project Office Establishment Regulations No. 84/2016; and

ሠ) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውበት፣ መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ ልማት እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፹፯/፪ሺ፱ አንቀጽ ፬(፯) እና (፱)፡፡

፫) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ የከተማው አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፲፯. <u>የተሻሻሉ የሕግ ድንጋጌዎች</u>

፩) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) የከተማው አስተዳደር ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ስልጣን እና ተግባሮች በተዘረዘሩበት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀፅ (፲፬) በመቀጠል የሚከተሉት ንኡስ አንቀጽ (፲፭)፣ (፲፮) እና (፲፯) ገብተዋል፡-

፲፭) በዘላቂ ማረፊያ የሚፈፀሙ ቀብሮችን መረጃ ይይዛል፣ ያጠናቅራል፤የቀብር ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤የአፅም ዝውውር ፈቃድ ይሰጣል፤ የባይተዋር ቀብር ያስፈፅማል እንዲሁም የአንቡላንስ መኪና ክራይ አገልግሎት ይሰጣል፤ለሚሰጡ አገልግሎቶች ተገቢውን ክፍያ በሕግ መሠረት ይሰበስባል፡፡

፲፮) በበጎ አድራጎት ማህበር ወይም ድርጅት ውስጥ ቆይተው በሞት የተለዩ እና ቀባሪ የሌላቸው ባይተዋሮች አስክሬኖች በአግባቡ እንዲከፈኑ እና እንዲቀበሩ እንዲሁም መረጃዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣

e) Articles 4 (7) and (9) of the Addis Ababa City Government Parks and Cemeteries Development and Administration Regulations No. 87/2017.

3) Any proclamation, regulations, directive or practice, which is in conflict with this proclamation, shall not be applicable to the matters provided for by this proclamation.

**17. <u>Amended Legislations</u>**

**1)** the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Organs Reestablishment Proclamation No. 35/2011 (as amended) is hereby further amended and new sub-Articles (15), (16) and (17) are added following sub-Article (14) of Article 47 pertaining to the powers and functions of the Labour and Social Affairs Bureau :

15) Handle and consolidate data concerning funerals carried out within cemeteries ensure that the funerals of unattended corpses are carried out, issue funeral certificates and permits for the transfer of buried corpses, provide ambulance transport rental service, and charge fees for the services it renders according to law;

16) Ensure that the funerals of the corpse of those who have stayed under the care of charitable associations or institutions but have no one to look after their funeral are properly covered and carried out, and information thereof is given properly;

፲፯) የዕድር ምክር ቤቶች በዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረገ ጥናት እንዲያደርጉ ይደግፋል፤ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴዎችን በመጠቀም የቀብር አገልግሎት ጥያቄ ከተሟላ መረጃ ጋር እንዲቀርብ እና አገልግሎቱ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

17) Support councils of funeral associations to conduct studies on the needs of the society regarding cemeteries, ensure that requests for funeral services are presented with the complete data thereof and services are provided by making use of modern methods of information management.

፪) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺህ፬ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺህ፮ አንቀፅ ፫(፯) ስር በተሻሻለው የከተማው አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣንን ኃላፊነቶች የሚዘረዝረው አንቀጽ ፵፬ (ሀ) እስከ (ሐ) ድንጋጌዎች እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡-

2) The Addis Ababa City Government Executive and Municipal Organs Reestablishment Proclamation No. 35/2011 (as amended by Article 3 (7) of Proclamation No. 43/2014) is hereby further amended and the following new sub-Articles (a), (b) and (c) are added under Article 44 on the Powers and Functions of the Addis Ababa Road Authority:

ሀ) አዳዲስ መንገዶች ሲሰሩም ሆነ ነባር መንገዶች ሲስፋፉ ለአረንጓዴ ልማት በከተማው ፕላን በተመለከተው መሰረት በቂ ሥፍራ እንዲዘጋጅ እና እንዲከለል ያደርጋል፤

a) Ensure that sufficient site is prepared and reserved for green development wherever new streets are designed and constructed or existing streets are expanded as envisaged by the urban plan;

ለ) በዋና መንገዶች እና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራ እና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮች እና አደባባይ ላይ የአረንጓዴ ልማት ስፍራዎች ዲዛይን የመንገድ ግንባታ ፕላን አካል አድርጎ በማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ መትከያ ስፍራዎችን ዝግጁ ያደርጋል፣ አስፈላጊውን መረጃ ለኤጀንስው በወቅቱ ይሰጣል፤

b) Prepare and reserve or ensure the preparation and reservation of plant growing sites on both sides, divides and squares of arterial and sub arterial streets by making their designs as part of the construction plans of such streets, and provide the necessary information thereof to the Agency timely;

ሐ) የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርድ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳር፣ አካፋይ እና የአደባባይ ዕጽዋት እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲ መወገዳቸውን ወይም መመልመላቸውን ያረጋግጣል፡፡

፫) የጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፪ሺህ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

ሀ) በአንቀጽ ፫(፪) የተደነገገው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

፪) ማዕከሉ ለኤጀንሲ ተጠሪ ይሆናል

ለ) በአንቀጽ ፲(፩) የቦርድ አባልነትን በሚመለከት ከፊደል (መ) ጀምሮ ያሉት ፊደላት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ከፊደል (ሠ) እስከ ፊደል (ቸ) ተሸጋሽገው የሚከተለው አዲስ ፊደል (መ) ገብቷል፡-

መ) የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር፡፡

## ፲፰. <u>የመብት እና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺህ፫ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፶፮ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር የውበት መናፈሻ እና ዘላቂ ማረፊያ ልማት እና አስተዳደር ኤጄንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኤጀንሲ ተላልፈዋል፡፡

c) Ensure that plants that tamper with the long sight of drivers or dried plants on the sides, divides or squares of streets are removed or pruned by the Agency timely.

3) The Gulele Botanical Garden Establishment Proclamation No. 18/2009 is hereby amended as follows:

A) The provision of Article 3 (2) is replace by the following new Article 3 (2)

2) The Centre shall be accountable to the Agency;

B) The provisions of sub-Articles (d) up to (k) of Article 10(1) are hereby rearranged ( e) up to (l) and the following new sub-Article (d) is added: (d) the Executive Director.

## 18.<u>Transfer of rights and obligations</u>

The rights and obligations of the Addis Ababa City Government Beautification, Parks and Cemeteries Development and Administration Agency established by the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Organs Reestablishment Proclamation No. 35/2011 (as amended) are hereby transferred to the Agency established by this Proclamation.

## ፲፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ኤጀንሲው በአግባቡ ተደራጅቶ በተሟላ ሁኔታ ስራ እስኪጀምር ድረስ በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) የተቋቋመው የከተማው አስተዳደር የውበት፣መናፈሻ እና ዘላቂ ማረፊያ ልማት ኤጀንሲ በመከናወን ላይ ያሉ ስራዎችን እያከናወነ ለርክክብ ዝግጁ ያደርጋል፤ በከንቲባው በሚሰጠው አቅጣጫ በሚወሰነው መሰረት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኤጀንሲ በስድስት ወር ውስጥ ያስረክባል፡፡

## ፳. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩) የከተማው ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ያወጣል፤

፪) በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው በግልጽ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ኤጀንሲው ዝርዝር የአሰራር ስነ ስርዓቶችን እና ቴክኒካዊ ጉዳዮችን የሚወስን መመሪያ እንዲያወጣ መደንገግ ይችላል፡፡

## 19. Transitional Provisions

The Addis Ababa city Government Beautification, Parks and Cemeteries Development and Administration Agency established by the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Organs Reestablishment Proclamation No. 35/2011 (as amended) shall carry on with performing its tasks and become ready to transfer same until the Agency established by this Proclamation is properly organized and resumes performing its work completely, and it shall finally hand over to the Agency established by this Proclamation within six months whatsoever under its control according to the direction to be issued by the Mayor.

## 20.Power to issue regulations and Directives

1)The City Cabinet may issue regulations necessary to implement this Proclamation;

2) Without prejudice to the powers and functions of the Agency clearly stipulated by this Proclamation, the City Cabinet may be stow power on the Agency to issue directives that shall set out procedures of implementation and technical matters.

**፳፩. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ከጸደቀበት ከሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ሐምሌ ፲ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

21. **Effective date of the Proclamation**

This Proclamation shall be effective as of this day of July 17, 2018, the date on which it is promulgated by the city council.

**Addis Ababa July 17,2018**

**Direba Kuma**

**Addis Ababa City Mayor**